# "ድመት መንኩሳ ..."

ከገረመው ደፋሩ

ምንም ብትመነኩስ፣ ቆብ ብትደፋ ድመት፣
እያማለሁ ብላ፣ ብትጀምር ስግደት፣
ወተት ባይኗ ካየች፣ በቅርብም በርቀት፣
አመሏን አትረሳም፣ እስከ-ዕለተ ሞት።
        የልዴቱም ነገር፣ እንደ ድመቷ ነው፣
        ትንሽ ወተት ካየ፣ የሚቀማምሰው፣
        ወደዚያ መሄዱ፣ ፍፁም የማይቀር ነው።
እንደ ሌሊቷ ወፍ፣ ሁሉን ያታልላል፣
"ወፍ ነህ እንዴ?" ሲሉት፣ "እዩት ጥርሴን" ይላል፣
"አይጥ ነህ?" ሲሉትም፣ ክንፎቹን ያሳያል።
        ያ'ኔ ሕዝብ ተፍቶት፣ በክፉ አመሉ፣
        እንዳልተደበቀ፣ እንዳልጠፋ ሁሉ፣
        መናኛ፣ ማፈሪያ፣ በጣም የዘቀጠ፣
        ያለምንም ሀፍረት፣ እያጉረጠረጠ፣
        "አለሁ!፣ አለሁ!" አለ፣ ዓይኑን አፈጠጠ፣
        ትላንት ስለምርጫው፣ የተዛባ ሂደት፣
        ያለውን ዘገባ፣ ሲያጋልጥ ፊት ለፊት፣
        ልክ እንዳልነበረ (ኢፍትሐዊነቱን)፣ እያስተባበለ፣
        በደል ተፍጽሟል፣ ግፍ ነው እንዳላለ፤
ወዲያው ግልብጥ ብሎ፣ በአንድ ቀን ጀምበር፣
"ምርጫው አይደገም፣ ይቀበለው አገር፣"
እንዴት ሊል ይችላል?! በጤናው ነው እንዴ?!
ወይስ ተደለለ? ባስለመዱት ዘዴ?!
        ገና ከጅምሩ፣ ደፍሮ ሲደሰኩር፣
        እስከማውቀው ድረስ፣ ባለሁበት አገር፣
        ከውስጥም፣ ከውጭም፣ ህዝብ ደግፎት ነበር፣
        ወላዋይ፣ ደጅ ጠኚ፣ ዓላማ የሌለው፣
        እንዴት ሕዝብን ያማል፣ እውን በጤናው ነው?!
ሰላሳ አንድ ነጥብ፣ ባለው ዝርዝር "ጥናት"፣
በሙሉ ኮንኖ፣ የምርጫውን ሂደት፣
እንዴት ይቀበላል፣ ኢፍትሐዊ ውጤት?!
        ያኔ በድል ጊዜ፣ በዘጠና ሰባት፣
        ቅንጅት ሲከተል፣ የሕዝቡን ፍላጎት፣
        ዘሎ ሽንጎ ገባ፣ ለራሱ በማድላት፣
        "ያኑሁ ይባስ! ያሁኑ ይባስ!" ዘንድሮስ ለየለት።
የአንድነት ተውሳክ፣ የመለስ ባለሟል፣
እንዴት "አንድ ሁነን፣ አንታገል" ይላል፣
ደግሞ እንደ ቅንጅት፣ መድረክን ሊበክል?!
ከእንግዲህስ ይብቃው፣ ማንም አይታለል!
        ሕዝብን ከማታለል፣ ከ'ንግዲህ ይጠንቀቅ፣
        የሚጥሉለትን፣ ቁራሽ ይጠባበቅ።
የትግል ስልቱ ነው፣ ያዋጣል የሚለው፣
ሶስተኛው አማራጭ፣ ወላዋይነት ነው፣
የኢዴፓ አባል፣ በመላ ይወቀው።